# የሰው አገር ...

እውነቱ በፍቅር – ጓዘኛው ጋዜጠኛ

አውሮፓ

ለውጭ አገር ኑሮ(ለስደት) የሚዳርጉ ምክንያቶች የተለያዩ ቢሆኑም ጦርነት ፣ የተፈጥሮ አደጋ ፣ የትምህርት እድል ፣ የፖለቲካ ችግር ፣ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ፣ ጋብቻና የእድል እጣ ፕሮግራም በደምሳሳው ከሚጠቀሱት በርካታ ጉዳዮች መካከል ዋናዎቹ ናቸው

የስደት ሕይወት በየዘርፉ መልካምና መጥፎ ጎኑ አመዝኖ ማስደሰቱም ሆነ ማማረሩ አይቀርም በደፈናው ስደት የሕይወት ኪሳራ አሊያም የአዲስ ሕይወት ምዕራፍ መገለጫ ተደርጎ በመጥፎና በመልካም ጉኑ ሊታይ የሚችልበት ሁኔታ ነው ያለው

ይህ ጉዳይ ሰፊ ጥናታዊ ትንተና የሚያሻው እንደመሆኑ በዚህ ርዕስ ላይ ትኩረቱን ባደረገ ሌላ ዘገባ በዝርዝር መመልከት የሚቻል ሲሆን እኔ መነሻ ሃሳብ ወዳደረኩት ነጥቤ ልውሰዳችሁ

በዚህ አምድ ስር ሕይወት በሰው አገር ውስጥ ምን እንደሚመስል የተለያዩ ግንዛቤ የሚሰጡ ሁኔታዎችን በአጭሩ በመግለጽ እንዲሁም የአንዳንድ አገሮችን ማህበራዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማሳየት ለአንባቢያን የአስተያየትና የመወያያ መድረክ መክፈት ነው

ከየአገራቱ ሊጠቀሱ የሚገባቸው አንዳንድ ጠቃሚ ጉዳዮችና እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መነሻ ሆነው ሊቀርቡ የሚችሉ የስደት ሕይወት ተመክሮዎች በአጭሩ ይቀርባሉ እንደየሁኔታው ደግሞ አካባቢያዊ ቅኝትም እናደርጋለን

## ለዛሬ – ኔዘርላንድ/ሆላንድ

ሙሉ ስም – ዘ ኪንግደም ኦፍ ዘ ኔዘርላንድ
ሕዝብ ብዛት – 16.4 ሚሊዮን (UN, 2007)
ዋና ከተማ – አምስተርዳም
የዓለም አቀፉ የጦር ወንጀለኞች ፍርድ ቤት መቀመጫ – ሄግ
ስፋት – 41፣ 864 ስኴር ኪሎ ሜትር
ዋና ቋንቋ – ደች
ዋና ሃይማኖት – ክርስትና


GRONINGEN
GASSELTE
AMSTERDAM
ARNHEM
ANTWERPEN
MAASTRICHT

አገሪቱን ለየት ባለ ሁኔታ ከሚያስጠቅሷት ነገሮች መካከልም ፣

- የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ፈቃድ
- የአደንዛዥ እጽ ተጣቃሚነት
- የዝሙት ንግድ ህጋዊነት

**እርሻ**
ባለፈው አመት ውስጥ ብቻ አራት ነጥብ አራት ቢሊዮን ኪሎ ግራም የአትክልት ምርት በአገሪቱ ተመርቷል ከዚህ ውስጥ 35 ከመቶው ፐርሰንት በላይ የተመረተው በግሪን ሃውስ የመስታወት/የላስቲክ የእርሻ ቤቶች ውስጥ ሲሆን ኩከምበር የፈረንጅ ቃሪያ እና ቲማቲም በምርት መጠን ብዛት በየደረጃቸው ተጠቃሽ ናቸው



Greenhouse Farm

አንድ አራተኛውን ድርሻ የሚወስደው ደግሞ የሸንኩርት ምርት ነው እጅግ የሚገርመው የአገሪቱ 85 ከመቶ ፐርሰንት የእህል ምርት የሚመረተው በዚሁ የግሪን ሃውስ የእርሻ ቤቶች ውስጥ መሆኑ ነው

ከአጠቃላይ የሸንኩርት ምርት ውስጥ 70 ከመቶው ፐርሰንት ወደ ውጪአገር ለውጭ ምንዛሪ ገቢ ንግድ ይላካል

**ትምህርት**
በሆላንድ ተማሪዎች ለትምህርት ወጪያቸው የሚበደሩት ገንዘብ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ነው መረጃዎ የሚጠቁሙት በ2007 ብቻ ተማሪዎቹ በአጠቃላይ የተበደሩት የገንዘብ መጠን 2 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ዩሮ ሲሆን ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በ19 ከመቶ ፐርሰንት ጭማሪ ማሳየቱን ጉዳዩ ከሚመለከተው ተቋም የወጣ መረጃ ያመለክታል ከዚህ ውስጥ የከፍተኛ ተቋም ተማሪዎች የተበደሩት የገንዘብ መጠን ከሁለት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዩሮ በላይ ነው

በአገሪቱ ሁለት አይነት የትምህርት ብደር አገልግሎት አለ አንደኛው ዘ ፐርፎርማንስ - ርሌትድ ሎን የሚባለው ሲሆን በተማሪዎች የትምህርት ብቃት ላይ ተመስርቶ ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመረቁ ሙሉ ለሙሉ የብድር እዳው የሚሰረዝበት አሰራር ያለው ነው ሁለተኛው አይነት ደግሞ ብድሩ ሙሉ ለሙሉ መከፈል የሚገባው የብድር አግልግሎት ነው

ይኸው ተማሪዎች ለትምህርት ወጪያቸው የሚበደሩት ዓመታዊ የገንዘብ መጠን አድገት እያሳየ መቷል

ባለፈው ዓመት ውስጥ ዜሮ ነጥብ ቢሊዮን የሚጠጋ ዩሮ ለፐርፎርማንስ - ርሌትድ ሎን ተበዳሪ ተማሪዎች የዕዳ ስረዛ ነጻ ዋስትና የተሰጠ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ የተበደሩትን መልሰው መክፈል ከሚገባቸው ተበዳሪ ተማሪዎች ከዜሮ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን የሚበልጥ ዩሮ ተመላሽ ክፍያ ተሰብስቧል

**ስደተኛ**

ከአጠቃላይ የአገሪቱ ሕዝብ ብዛት ውስጥ የአገሬው የደች ተወላጅ ዜጋ ብዛት ሰማኒያ ከመቶ ፐርሰንት ፣ የሌላ አገር መጤ ስደተኞች ብዛት ደግሞ ሃያ ከመቶ ያህል ፐርሰንት እንደሆነ ይገመታል

ከዚህ የሃያ ከመቶ ፐርሰንት ያህል የሌላ አገር ዜጎች ብዛት ውስጥ የዘጠኝ ከመቶ ፐርሰንት ድርሻውን ከምዕራባውያን አገራት ውጪ እንደ ብዛት ቅደም ተከተላቸው የቱርክ ፣ የሞሮኮ ፣ የአንቲሊያንስ ፣ የሱሪናሚስና የኢንዶኔዥያ ተወላጆች ይወስዳሉ

የሌላ አገር ስድተኞች በከፊተኛ ቁጥር የሚኖሩባቸው አራቱ ከተሞችም አምስተርዳም ፣ ሮተርዳም ፣ ዘ ሄግና ኡትረችት በተራ ቅደም ተከተል ተጠቃሾች ናቸው



በዚህ ዓመት በመጀመሪያው የሩብ ዓመት አጭር ጊዜ ውስጥ ብቻ 35 ሺ ስደተኞች ከተለያዩ የዓለማችን አገሮች ወደ ኔዘርላንድ መግባታቸውን የአገሪቱ ስታስቲክ ቢሮ መረጃ ያመለክታል ይህ ቁጥር ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር የስድስት ሺ ቁጥር ብልጫ አለው

ከዚህ ውስጥ ደግሞ አሁን አሁን ከፈተኛውን ድርሻ ወስደው የሚገኙት የተለያዩ የአውሮፓ አገር ስደተኞች ሲሆኑ ፖላንዳውያን በቁጥር ብዛት የመጀመሪያውን ደረጃ ይወስዳሉ በዚሁ 2008 የሩብ ዓመት ውስጥ ወደ ኔዘርላንድ ከገቡት ስድተኞች መካከል አራት ሺ የሚጠጉት ፖላንዳውያን ናቸው

በአጠቃላይ ከሌሎች አውሮፓ አገሮች ወደ ሆላንድ ከሚገቡት ውስጥ ጀርመኖች ፣ ቤልጂሞች እና እንግሊዞችም ተጠቃች ናቸው

በአገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ ከሚኖረው አጠቃላይ ሕዝብ ውስጥ ከአስር ሰዎች መካከል ሶስቱ የሌላ አገር የትውልድ ዝርያ ያለባቸው እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ

በአጠቃላይ በአገሪቱ ከአንድ መቶ ሺ በላይ ስደተኛ ይኖራሉ ተብሎ ሲገመት ፣ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን በተመለከተ የቅርብ ጊዜ ስታስቲክ ለማግኘት ብቸገርም የGlobal Migrant Origin Database መረጃን መነሻ በማድረግ ከአስር ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን በሆላንድ እንደሚኖሩ ነው

የአገሪቱን ምድራዊ አቀማመጥ በመቃኘት ፣ የመሃል መዲናዋን አካባቢ በጥቂቱ ወደሚያስቃኘው እንዲሁም ለግንዛቤ የሚረዱም አንዳንድ የስደት ሕይወት ተመክሮዎችን ወደሚያቋድሰው ቀጣይ የብዕር ጠማሬ በዚሁ ላምራ

ሆላንድ ሰፋ ባለ ይዞታ ከባህር ወለል በታች የምትገኝ አገር ናት ፣ ከአንድ ሶስተኛ በላይ የአገሪቱ ክፍል ከባህር ወለል ብታች ሲገኝ ሃያ ከመቶውን ክፍል ደግሞ የሚሸፍነው ይኸው የውሃ ክፍሉ ነው

አብዛኛው የሰሜን የአገሪቱ የውሃ ክፍል ደግሞ በአፈር ደለል እየተሞላ የመሬት ክፍል እንዲሆን ተደርጎ ነው በሰው ሃይል የተሰራው

ወደፊት በውሃ ሙላት ይጥለቀለቁ ይሆናል ተብለው ስጋት ውስጥ ከገቡ የዓለማችን አገሮች ውስጥ ሆላንድ አንዷ ናት

በየትም አገር የስደት ሕይወት ሲታሰብ ሊጤኑ የሚገባቸው በርካታ መጥፎና ፈታኝ ሆኔታዎች መኖራቸውን ለማስገንዘብና ለማመላከት ያህል ፣

- የስራና የመኖሪያ ፍቃድ አለማግኘት
- የስራ እድል ማጣት
- የዘረኝነት መድልዎ
- የቤተሰብና ያገር ናፍቆት
- ከአዲስ ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ጋር ያለመላመድ ሁኔታ
- ቤተሰብን የመርዳት ፋላጎትና ጥረቱ ብሎም
- የጤና መታወክና የስነ ልቦና ቀውስ ችግሮች ተጠቃሽ ናቸው

ሆላንድ በስደት ሕይወት ለመኖር ሲመጣ በሃያዎቹ እድሜ ክልል ውስጥ ነበር የተሰፋ ብሩህ ሕይወት ሰንቆ ከአገሩ የወጣው ይህ ሰው ዓላማና ፍላጎቱን ምኞትና ፍቃዱን ለማሳካት ሲጥር ዘጠኝ ዓመቱን አስቆጥሯል

ዓላማውን ከግብ ለማድረስ እርሱ ቢፈልግም ፣ ምኞቱን ለማሳካት እርሱ ቢጥርም ሁኔታዎች ግን አልፈቀዱለትም አምስት አመት እስኪሞላው ድረስ የመኖሪያና የስራ ፍቃድ ወረቀት ስላልነበረው እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉትን እድሎች ለማግኘት አይችልምና ነው ፣ ለነገሩ እድሉ እያላቸውም ቢሆን በሚደርስባቸው የዘር መድሎ ምክንያት በደል እየተፈጸመባቸው ሊያገኙ የሚገባቸውን የስራ እድል የሚነፈጉ በርካቶች ናቸው

ይኸው ሰው የስራና የመኖሪያ ፍቃድ ወረቀቱን ያገኘው ከአራት ዓመት በፊት ነው ይሁን እንጂ በዛ ባሳለፈው የአምስት ዓመት የመከራ ሕይወቱ ግን ባጋጠመው የስራ ማጣት ፣ የዘር መድሎዎና የማግለል ሁኔታ ችግሮች በደረሰበት የስነ ልቦና ቀውስ ትዕግስትና ጽናቱን አጥቷል

ያለበትን ከፍተኛ ጭንቀትና ሃሳብ ያቃልልኛል በሚል ፣ ቀስ በቀስ የጀመረውን ሲጋር ወደ አደንዛዥ እጽ አሳድጎ ዛሬ ባለሱሰኛ ሲሆን እንደነገሩ ሰርቶ ከሚያገኛት አነስተኛ ገቢውም ከፊተኛውን ወጪ በሚወስድበት አደንዛዥ እጽ ራሱን ደብቆ ፣ ህሊናውን አናውዞ እቤት ካልገባ በስተቀር በጸጸትና በንዴት አንድ ቀን ራሱን እንዳያጠፋ ስጋት እንዳለው ለቀረበው ሰው ሁላ በሃዘን ያወራል

✲ ✲ ✲

በስደት ህይወቱ ብዙ ችግሮችን አሳልፏል አሁን የሚገኘው በሰላሳዎቹ መጨረሻ የዕድሜ ክልል ውስጥ ሲሆን ስደት ለእርሱ ታላቅ የሕይወት ትምህርት ቤትም ነው

በዚህ እጅግ ፈታኝ የስደት ሕይወቱ ተደስቶ አዝኗል ፣ አግኝቶ አጥቷል ፣ ስቆ አልቅሷል ፣ ተጽናንቶ ተማሯል ፣ ታግሶም ተስፋ ቆርጦም ያውቃል ይሁን እንጂ ዓላማውን ለማሳካት ሁሌም ከመትጋት አልተቆጠበም

አገር ቤት ሳለም በልጅነቱ ይመኝ የነበረውን ለመሆን የሚያስችለውን የትምህርት እድል አግኝቶም ስራ ሳይንቅ ያገኘውን አይነት ስራ እየሰራ የተሻለ ደረጃ ለመድረስ በትጋት ጸንቷል ከአልባሌ አሳሳች ድርጊቶች ራሱን በማግለል የጋጠሙትን ፈታኝ የሕይወት ውጣ ውረዶች በትዕግስትና በመንፈስ ጠንካራነት እየወደቀም እየተነሳ በድል አድራጊነት ተወጥቷቸዋል

የጀመረውን የኤሌክትሪክ ኢንጅነሪንግ ትምህርት አንዳንዴ ጊዜ በማይሰጡ ጠንካራ የሕይወት ገጠመኞች ሲገደድ እያቋረጠ ሲመቸው ደግሞ እየቀጠለ ለማጠናቀቅ በቅቷል ዛሬ በዚሁ በተመረቀበትና ከልጅነቱ ይመኘው በነበረው ሙያ በአምስተርዳም አየር መንገድ ኤለክትሪሻን ኢንጅነሪንግ ሆኖ በከፈተኛ ደሞዝ እየሰራ ይገኛል

ከራሱ አልፎ ለቤተሰቡ ብሎም ለአገሩ እጅግ የሚያኮራ እንዲሁም በስደት ሕይወት ለበዙዎች መልካም አርአያ ለመሆን በቅቷል ይህ ሰው ከአገሩ ሴት ጋር ትዳር መስርቶ የአንድ ወንድ ልጅ አባትም ነው

❊ ❊ ❊

አገር ቤት እያለች ምንም ያልጎደለባት ፣ ደህና ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ያልዋት ፣ ትምህርቷንም እስከዩኒቨርስቲ ለማጠናቀቅ የበቃች ልጅ ናት እዚህ ሆላንድ አገር ከዘመድ በተላከ የጉብኝት ቪዛ ትመጣና ልመለስ ወይስ ልቅር በሚል ጥያቄ ስታመነታ የጉብኝት ቪዛዋ ያልቃል

በአንድ በኩል የመመለሷን ነገር እንዲሁ ስታወጣ ስታወርድ በሌላ በኩል ደግሞ ይህን እድል ለተሻለ ነገር ልጠቀምበት በሚል ፍላጎት የስራና የመኖሪያ ፍቃድ ለማግኘት አመልክታ መልስ ስትጠብቅ ሶስት ዓመት አለፋት

ደህና ስራ ተቀጥሮ ለመስራት ህጋዊ ወረቀት የሚያስፈልግ በመሆኑ ስላልሆነላት ጥቁር ስራ (በድብቅ ያለ ሙሉ የስራ ዋስትና የሚሰራ ስራ) በተባራሪ እዚህና እዚያ እየሰራች ለመኖር ያህል አለች

❊ ❊ ❊

የስደት ሕይወቷ በአገሯ ሳለች ከልጅነት ብሎም እስከ ከፍተኛ ትምህርት የነበራትን ህልም እንዳመከነባት አሁን በጸጸት ትናገራለች አትመለስ ነገር አንድ ጥሩ ነገር ሳልይዝ እንዴት የሚል ሙግት ውስጥ ትገባለች፣ ከዛሬ ነገ ህጋዊ የመኖሪያና የስራ ፈቃዴን አግኝቼ የተሻለ ሕይወት ይገጥመኛል በሚል ተስፋ ደግሞ አሁን ባለችበት ሁኔታ በስደት ትኖራለች



**Amsterdam (From in Front of the Train Station)**

አምስተርዳም በዓለም አቀፍ ደረጃ በብዙ መልካምና (በመጥፎ) ጎኑ የገነነች መዲና ናት

በዚች ጉድ በምታሰኝ አገር ዋና ከተማ ሊያደርጉት የሚፈልጉት ማናቸውም አይነት ነገር በምርጫ እንደሚቀርብሎት ነው የሚነገረው የአደንዛዥ እጽ ፣ የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ፣ የወሲብ ንግድ ፣ የአደገኛ መጠጦች ሽያጭ ፣ ቁማር በየአይነቱ ደቂቃዎች ብቻ በሚፈጅ የእግር ጉዞ በየቦታው ያገኛሉ

ታድያ የዚያኑ ያህል ከዚህ ሕይወት ፈጽመው ርቀው ሰላማዊ ኑሮ የሚኖሩ ሰዎችና መኖሪያ አካባቢዎች መኖራቸውም ሳይዘነጋ ነው

መዲናዋን ለመጎብኘት እድል የገጠመው አንድ የራሱ ባህል ያለውና የተለየ የአኗኗር ዘይቤ ተከትሎ ያደገ እንግዳ ጉድ የሚሰኝባቸው ክስተቶች ሞልተዋል

የአድንዛዥ እጽ ገዝቶ ለመጥቀም ልክ ከረሜላ ከሱቅ እንደመግዛት ያህል ፣ የቀይ መብራት ቤቶች ብዛትና የሴቶቹ እራቁት እየሆኑ በመስታወት ቤት ውስጥ እንደ ልብስ ሽያጭ ተኮልኩለው ማየት ልክ በግ ተራ ወርዶ ጠቦት የመግዛት ያህል ፣ የወሲብ ኢንዱስትሪ ዘመናዊነትና ትዕይንቱ ደግሞ የሶዶምና ጎመራ ታሪክን ለሚያስታውሰው እንደ እኛ አገር ላለ ሃይማኖተኛ እንግዳ ደግሞ የስምንተኛው ሺ ዘመን መቃረቡን ይረዳ ይሆናል




በከተማዋ ከአነስተኛ ወንዝና ሃይቅ መሰል ትንንሽ ጅረቶች ጀምሮ እስከ ወደብ ደረጃ የሚያገለግል የባህር ክፍል ይገኛል ለነዋሪው ነጻ ትራንስፖርት የሚሰጡና ለቱሪስት አገልግሎት የሚንቀሳቀሱ በረካታ ጀልባዎችን በመዲናዋ ዙሪያ ማየት ልክ እንደ አገራችን ታክሲዎች የተለመደ ነው

አገሪቱ በወደብ አገልግሎት በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ስትሆን የአምስተርዳም ወደብ ሰፊ አገልግሎት ይሰጣል ከተለያየ የዓለማችን ክፍል የተለያየ አገር ባንዲራ የሰቀሉ እጅግ ግዙፍ የዕቃና የመንገደኛ መርከቦች እምብርት መዲናዋን በሚታከከው የባህር ክፍል ሲተላለፉ ማየት ራሱን የቻለ ልዩ ትዕይንት ነው



Port of Amsterdam

ይህ እንግዲህ በከተማዋ ከሚርመሰመሱት ተሽከርካሪዎች ፣ አውቶብሶች ፣ የኤሌክትሪክ ባቡሮች በተጨማሪ ሲሆን እዛው መሃል መዲና የአገሪቱ ዋናው አገር አቋራጭ የባቡር ጣቢያ ይገኛል በዚህ የባቡር ስምሪት ጣቢያ ውስጥ ሁሉ ነገር አለ ማለት ይቀላል ከትንንሽ ሱቆች እስከ ባንክ ፣ ከካፌ እስከ ትላልቅ ሬስቶራንቶች አገለግሎት ይሰጣሉ

በየቦታው የውጭ ምንዛሪ አገልግሎት ያለምንም ችግር የሚሰጡ ትንንሽ ሱቆችንም ማግኘት ይቻላል

በመዲናዋ ለተሽከርካሪዎች እንደዓይነታቸው ፣ ለእግረኞችና ብስክሌተኞች ጭምር ራሱን የቻለ የተለየ መንገድ ተገንብቷል

እግረኞች ብቻ የሚተላለፉበት ሰፋፊና ያማሩ የመንገድ ግንባታዎቹም የስልጣኔያቸው መገለጫ ነው ለየብቻ የተሰራው ይኸው የእግረኛውና የብስክለተኛ መንገድ በየቦታው ያለ ሲሆን በተለይ በመደብሮች ፣ በመዝናኛ ቤቶች ፣ በምግብና መጠጥ ቤቶች እንዲሁም በተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎት በሚሰጡ ተቋሞች የተማከለው የመሃል መዲናዋ የ Shopping Street አካባቢ እግረኛ መንገድ ይማርካል


Amsterdam Shopping Street

በአካባቢው ከተሽከርካሪ ጋር ሳይጋፉ እጅግ በርካታ እግረኞች ለተለያየ ጉዳይ በየቀኑ ግራና ቀኝ በስነ ስራዓት ይርመሰመሳሉ

የሆላንድ ነዋሪዎች በእጅጉ የሚታወቁበት አንድ ጉዳይም አለ – ብስክሌት በብዛት ተጠቃሚ መሆናቸው በመዲናዋ አምስተርዳም ከመኪና ይልቅ በብስክሌት ቢዟዟሩ ከተማዋን በደንብ ለመጎብኘት የሚያስችል ሲሆን በየቦታውም እጅግ በርካታ ብስክሌቶች ይታያሉ



በመሃል ዋና ከተማዋ እጅግ ዘመናዊ የሆኑ ሱቆች ፣ ባርና ሬስቶራንቶች ፣ የሃሽሽ መሸጫ – coffeehouse/shop የንግድ መደብሮችና ማጨሺያ ቤቶች እንዲሁም የቀይ መብራት የወሲብ ንግድ ስፍራ በብዛት የሚገኝበት አካባቢም አለ

በተለይ ይህ የሴክስ ቱሪዝም ንግድ በሰፊው የሚካሄድበትን የቀይ መብራት አካባቢ በቃላት ለመግለጽ እጅግ ይከብዳል – ዘመናዊው የውቤ በረሃ ሰፈር ብለው ምናልባት አንባቢዎቼ ምናባዊ ግንዛቤ ያገኙ ይሆናል

በዚህ የሴክስ ንግድ ኢንዱስትሪ ስራ ላይ የተሰማሩ ሴቶችን በየቀለም አይነቱ መብራት አጊጠው በመስታወት ውስጥ መለመላቸውን የሚያይ እንደእኛ አገር ያለ ሰው ንስሃ የሚገባው ወዲያውኑ ነው

ሴቶቹ እንደዓለም ክፍላችን አገራት በቀለም በዘር በቅርጽና በመጠን የተለያዩ ናቸው - ዋጋቸውንም እንደዛው በነጻ ገበያ እንደሚፈለጉት አይነት አገልግሎት መደራደር ይቻላል

ይህ አካባቢ በተለይ በብዙ ቁጥር ቱሪስቶች የሚዘወተር ሲሆን የሚጎበኝም ነው ገንዘብ ከፍለው ልክ እንደ ቲያትር በተግባር የሚከናወን ፤ የሚተወን የወሲብ ግንኙነት የሚመለከቱባቸውም ቦታዎችም አሉ እነዚህ አካባቢዎች ታዲያ ሽቀጣ ሽቀጥ ፤ ምግብና አልባሳት ከሚሸጥባቸው መደብሮች ይልቅ በብዛት የሚገኙት ለዚሁ የጾታ ግንኙነት የሚያገለግሉ መጠን ፤ አይነትና ቅርጻቸው የተለያዩ የሴትና የወንድ ሰው ሰራሽ የአፍረተ ስጋ ቁሳቁሶችና መድሃኒቶች ፤ እንዲሁም የአድንዛዥ እጾች በህጋዊ መንገድ በግልጽ የሚሸጥባቸው ሱቆች ናቸው



Red light district, Amsterdam

በእነዚህ ጎዳናዎች አካባቢ አንዳንዴ በእግር ቢጉዋዙ ንጹህ አየር ለመተንፈስ ይቸገራሉ በአካባቢው የአድንዛዥ እጽ ንግዱ ከመስፋፋቱና ከተጠቃሚው ቁጥር ብዛትም የተነሳ ከአጫሹ አልፎ ተርፎ ለአላፊ አግዳሚው በትንፋሽ መዳረሱ ምን ያህል ችግሩ ስር እንደሰደደ ለመረዳት አይቸገሩም

በዚህ አካባቢ መተላለፍ የሚያዘወትሩ ጤነኞችም ሳይወዱ በግድ በሚተነፍሱት ዓየር ብቻ የነገሪቱን እፍታ ተቋዳሽ እየሆኑ ዝም ብለው ፈገግታ የሚያበዙ መኖራቸውንም አንዱ ወዳጄ እንደቀልድ አውግቶኛል

እነዚህን ነገሮች ማንሳቴ በሃገራችን ባህልና እምነት እንዲሁም ስነምግባር አድገው ኖረው በስደት ሕይወት ውስጥ ደግሞ ይህን በመሰለ እጅግ ተቃራኒ ማህብረሰብ ወስጥ ሲቀላቀሉ ሊገጥም የሚችለውን ማህበራዊ ችግር አንባቢዎች እንድታጤኑት ፈልጌ ነው

ይህ ብቻ ሳይሆን በዚህ ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን በመልካም ምግባርና ስራ አንጸው ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሱና ፤ እየጣሩ ያሉ የመኖራቸውን ያህል ለዚያ የቀይ መብራት የወሲብ ንግድ ሰለባ ሆነው ለከፋ ሕይወት የተጋለጡ እህቶቻችን እንዲሁም የአድንዛዥ እጽ ተጠቃሚ በመሆን የባዘኑና የገዛ ሕይወታቸውን ያጡ ወንድሞቻችን መኖራቸውን ልብ እንድትሉ ነው

አስተያየትና ህሳብ በመለዋወጥ ልትወያዩበት ትችሉ ይሆናል

ቸር ይግጠመን !

ewnetubefiker@yahoo.com